የሰ/መ/ቁ. 48018

ሐምሌ 7 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ተከተል ዘካሪያስ - ወኪል አዳነች ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1. ወ/ሮ አስቴር ታደሰ - ጠበቃ አቶ ፍቃዱ ያሚ ቀረቡ

2. አቶ ገነነ ደምሴ - በሌሉበት ይታያል

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቹ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው ስለጠየቁ ነው፡፡ በሥር ክርክሩ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነ ተሽከርካሪ በሁለተኛ ተጠሪ ሹፌርነት ሲሽከረከር በሰበታ ሐዋሳ ወረዳ ቀበሌ 01 ገጭቶ ጉዳት ያደረሰብኝ ስለሆነ ካሣ ይከፈለኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካች ክሱን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 መሰረት ጉዳቱ በደረሰበት ቦታ የሥረ-ነገርና የክልል ግዛት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለባቸው በማለት ተቃውመዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ጉዳዩን ለማየት የግዛት ክልል ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያቅርብ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይኑ በይግባኝ መርምሮ አጽንቷል፡፡

አመልካች በሁለት ክልል ኗሪዎች መካከል የሚነሣው ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መታየት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 25/88 ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 10 እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 19 ሊወድቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ጉዳቱ የደረሰበት ቦታ ብቻ ነው መክሰስ ያለባቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል አንደኛ ተጠሪ በበኩላቸው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 በጉዳት ካሣ ጊዜ የክልል ሥልጣን ያለው የትኛው የፍርድ ቤት እንደሆነ የሚደነግግ ልዩ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የሕግ ትርጉም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡

በሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አከራካሪው ጭብጥ ጉዳዩን የማየት የግዛት ክልል ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የትኛው ነው? የሚለው ነው፡፡ በመርህ ደረጃ በሰዎች ወይም በሚንቀሣቀስ ሐብት ላይ በደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስ ጉዳቱ በደረሰበት ሥፍራ የሥረ-ነገረ ሥልጣን ሳለው ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ይህም የሆነው የደረሰው የጉዳት እና ከጉዳቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ጉዳቱ በደረሰበት አካባቢ በቀላሉ ማስረጃ ለማግኘትና ማስረጃም ለማቅረብ የሚቻል በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ከላይ የተገለውን የሕጉን ዓላማ በአግባቡ ማሣካት የማይከለክል በሆነ ጊዜ በሰው ወይም በሚንቀሣቀስ ንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስ ተከሳሽ በሚኖርበት ቦታ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ጉዳቱ የደረሰው ሰበታ አካባቢ መሆኑ የተጠሪዎች የመኖሪያ ቦታ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መሆኑና ምስክሮችና ሌሎች ማስረጃዎችን ለማቅረብ የሚያጋጥም የትራንስፖርትና ሌሎች ችግሮች ቀላል በመሆኑ አመልካች ክሱን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማቅረባቸው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ የሚቃረን ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎና አከራክሮ በፍሬ ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት ሲገባው የግዛት ክልል ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ስህተቱን ማረም ሲገባው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይንና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የክልል ግዛት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪዎች በፍሬ ጉዳይ ላይ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 341 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መልሰንለታል ይፃፍ፡፡

በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ